

# መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ-ምግባራት
# ክፍል ፩


በአባ ኃይለ ገብርኤል ግርማ

ሸፊልድ - ሊድስ



# መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ-ምግባራት

- መጽሐፍ ቅዱስ ለምን የተለየ የሕይወት መጽሐፍ ተባለ?
- መጽሐፍ ቅዱስ ለምን በዓለማችን አስፈላጊ ሆነ?
- መጽሐፍ ቅዱስ ከሥነ-ምግባር ጋር ያለው ግንኙነት?
- ሥነ-ምግባር ማለት?
- የሥነ-ምግባር መሰረታዊ ነጥቦች?



# መጽሐፍ ቅዱስ ለማጥናት?

| | ምንጩን ለመረዳት | ይዞታውን ለመረዳት | ትርጉሙን ለመረዳት |
|---|---|---|---|
| ማን? | ማን ጽሑፉን ጻፈው? | ጽሑፉ ማንን ያሳያል? | ጸሐፊው ምንን የገልጻል? |
| ምን | በጽሑፉ ውስጥ ምን ተከናውኗል? | ምን ዓይነት የአጻጻፍ መንገድን ተከትሏል? | በጽሑፉ ውስጥ ምን ዓበይት ኀሳብ አለ? |
| ለምን? | ለምን ተጻፈ? | ለምን ዝግጅት የቀረበ ነው? | ጸሐፊው ቃላቶቹንና ስንኞቹን ለምን ተጠቀመመባቸው? |
| መቼ? | መቼ ተጻፈ? | መቼ በተግባር ላይ ዋለ? | መቼ ሥርዓትን የተከተለ የዕቅድ ሥራ ታየ? |
| እንዴ ት? | እንዴት በአንድነት ተጠረዘ? | ተጠቃሚው እንዴት ይጠቀምምበታል? | እንዴት በሕይወት መተርጎም ይቻላል? |



# ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት?

1. ባለተለመደ ቋንቋ መጻፉ
2. ባለሙያዎች ብቻ የሚረዱት
3. ጊዜ የሚጠይቅ
4. የማይሰለችና የሚደጋገም
5. ትልቅ፡- 750,000 ቃላት፣ 1,189 ምዕራፍ፣ከ40 ያላነሱ ጸኃፊያን፣ 1000 ዓመታት
6. ጉዳዩ፡- ለሁሉም፣ ታሪካዊ ጥቅም፣ ታላላቅ ጥያቄዎችን የሚያነሳ የእግዚአብሔር ቃል



# መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ

- አክብሮት------ ራስን ከመጠየቅ ጋር
- ጸሎት
- ዕቅድ ማውጣት
- ኃይለ ቃላትን መያዝ
- ታሪካዊ ሂደትን መመልከት
- ባህልንና የአካባቢውን ዕውቀት ማመዛዘን
- ጥበብን መጠቀም



# የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍላት

1. ብሉይ ኪዳን

   ዕብራውያን መጻሕፍት

   1ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ

2. ሐዲስ ኪዳን

   ወንጌላትና መልእክታት

   4ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ





# ዕብራውያን መጻሕፍት → ወንጌላት→ መልዕክታት

⌖ ዕብራውያን መጻሕፍት ክፍላት

1. የሕግ መጻሕፍት
2. ቀደምት ነቢያት
3. ቀደምት ጸሑፎች
4. የኋላ ጹሑፎች
5. የኋላ ነቢያት/ ደቂቀ ነቢያት

⌖ ወንጌላት

1. ማቴዎስ
2. ማርቆስ
3. ሉቃስ
4. ዮሐንስ

⌖ መልዕክታት፡- የጴጥሮስ፤ የጳውሎስ፤ የዮሐንስ፤ ያዕቆብ፤ይሁዳና ራዕይ ዮሐንስ



# ሥነ-ምግባራት

- የግዕዝ ቃል "ሥን" — "ሠነየ" -- አማረ፣ መልካም ሆነ
- "ምግባር" --- "ገብረ" --- ሠራ
- በተናባቢ --- በሥራ ማማር
- በቅጽል --- ያማረ ሥራ፤ መልካም ሥራ

"ፍቅረ-እግዚአብሔር ካለ ሥነ-ምግባር አይገድም።"



# ዐበይት ሥነ-ምግባራት (CARDINAL VIRTUES)

1. የግል ሥነ-ምግባራት (Personal Virtues)

- ራስን መቆጣጠር (Temperance)
- ታታሪነት (Courage)
- ጥበብ (Wisdom)

2. የጋራ ሥነ-ምግባራት (Social Virtues)

- ቅን ፍርድ (Justice)
- ደግነት (Active Kindness)

3. ሃይማኖታዊ ሥነ-ምግባራት (Religious Virtues)

- እምነት (Faith)
- ተስፋ (Hope)
- ፍቅር (Love)



# ራስን መቆጣጠር Temperance [Self-control]

- ራስን መግዛት ውሳጣዊ ህሊናን መቆጣጠሪያ ልዩ ስጦታ (ችሎታ) ነው።
- በሥነ-ልቡና ሕይወት ራስን መግዛት ማለት፡- ራስን ከክፉ ተግባራት መለየት፤የመምረጥ ነፃነትን በመጠቀም የቆራጥነትን ሕይወት መያዝ ነው።



- በግሪክ (εvκρατεια) enkrateia (adj.)
- (Ενκρατευομαι) Enkrateuomai [v.] ቃሉን ለመጀመርያ ጊዜ በኦሪት ዘፍጥረት 43፡31 ዮሴፍ ወንድሞቹን ባገኘ ጊዜ የተጠቀመበት ዘዴ
- ቅ. ጳውሎስም ራስን ስለመቆጣጠር 1 ቆሮ.7፡5-7
- “The Greeks held temperance to be a cardinal virtue.”



- ራስን መግዛት ከእውነት (ከጽድቅ) ጋር ተገልጿል። ሐዋ. 24፡25
- በሐዲስ ኪዳን፡- '…fruit of the Spirit.' ገላትያ 5፡22-23 '…drink of the Spirit.' 1ቆሮ.12፡13
- የመንፈሳዊ ሕይወት መንገድ - ሐዋ.2፡15-17፤ ኤፌ. 5፡18
- የሥነ-ምግባር ውጤት 2 ጴጥሮስ 1፡6
- በአእምሮ ዳኝነት መኖር



# ራስን መቆጣጠር ከምን?

- በአእምሮ ዳኝነት በመታገዝ ሰብእናን፣ ነፃነትን፣እኩልነትን ከሚጋፉ፡-
  - በመናገር
  - በማሰብ
  - በተግባር በመግለጽ የሚቀርቡ
    - ቁጣ
    - ሀሜት
    - ሱሰኝነት



## “ሢም እግዚኦ ዐቃቤ ለአፉየ” አቤቱ ለአፌ ጠባቂ አኑር። መዝ. 140፡3

መጽሐፍ ቅዱስ በአንደበት የሚፈጸሙ ኃጢአቶች በተመለከተ፡-

- “ሕይወትና ሞት ከአንደበት እጅ ናት።” ሲራክ 18፡21
- አንደበት ለውድቀትና ለሞት- ሲራክ 22፡27
- “አንደበቱን ሳይገታ እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሚመስለው ሰው ማንም ቢሆን አምልኮቱ ከንቱ ነው።” ያዕ. 3፡6
- “በአንደበቴ እንዳልስት አፌን እጠብቃለሁ” መዝ.38፡1



# ሀሜት

- ወንድሙን የሚያማ ሕግን ያማል።” ያዕ.4፥11 ዘኊ.12፥1
- “አንተ ለምን በወንድምህ ላይ ስለምን ትፈርዳልህ ወይስ አንተ ደግሞ ወንድምህን ስለምን ትንቃልህ? ሁላችን በክርስቶስ ወንበር ፊት እንቆማለን።” ሮሜ14፥14



- በሀሜት ውስጥ፡-

—ስድብ “ተሳዳቢዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።” 1ኛቆሮ.6፡10

—ወሬ “ጠማማ ሰው ጥልን ይዘራል ጆሮ ጠቢ ሰው የተማመኑትን ወዳጆች ይለያያል።” ምሳ.16፡28

—መርገም “ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ።” ያዕ.3፡10

—አሽሙር “በሰነፍ አፍ የትዕቢት በትር አለ።” መዝ.140፡3

—መሳለቅ “በደሀ የሚያላግጥ ፈጣሪውን ይሰድባል።” ምሳ.17፡5

—መዋሸት “ውሸተኛ ከንፈር በእግዚአብሔር ዘንድ አጸያፊ ነው።” ምሳ.12፡22

—ማስደንግጥ “ያዘነ ልቡናን አታስደንግጥ።” ሲራ.4፡3

—መዳፈር “ሰነፍ ደፋር ሰው ግን እንዳገኘ ይናገራል።” ሲራ. 20።7



# ቁጣ

- ከቁጣ ይልቅ ለትዕግስት ሰፊ ጊዜን መስጠት
- “ለትዕግስተኛ ሰው ብዙ ማስተዋል አለው፤ ቁጡ ግን ስንፍናውን ከፍ ከፍ ያደርጋል።” ምሳ. 14፡2-29
- “ቅንዓት ለሰው የቁጣ ትኩሳት ነው።” ምሳ.6፡34
- “የለዘበች መልስ ቁጣን ትመልሳለች፤ ሻካራ ቃል ግን ቁጣን ታስነሳለች።” ምሳ. 15፡1
- “ከቁጣ ራቅ መዓትንም ተው እንዳትበድል አትቅና።” መዝ.36(37)፡8



## ራስን ባለመቆጣጠር የሚከሰቱ ችግሮች

- ፈተና (massa [EVV] Hebrew ‘temptation’)

1. መልካም ፈተና 1ቆሮ.11፡28፤ 2ቆሮ.13፡5፤ ያዕ.1፡2/12፤ ዘፍ.22፡1
2. ክፉ ፈተና 1ጴጥ.5፡9 ኤፌ.4፡27፤ 1ቆሮ.7፡5



# በኅሊና የሚፈጠሩትን የፈተና መንገዶች መቃወሚያ

1. የተፈጥሮ የሥነ-ምግባር መመሪያ
2. የታላላቅ ዝንባሌዎች እውቀት
3. ተጨባጭ ግንዛቤዎች

“እንታገስ ዘንድ እንድንችል ከፈተናው ጋር መውጫውን ለሚያደርግልን ለአምላካችን ለልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይሁን።” 1ቆሮ. 10:13



# ከፈተና ለመውጣት፡-

- ዲያብሎስን መቃወም--- ያዕ.4፥7
- ከምንፈተንበት መራቅ--- 2ጢሞቴዎስ 2፥22
- ቅድመ ዝግጅት ማድረግ
- በመልካም ተግባራት ጋር መዛመድ
- አእምሮንና ልብን ለእግዚአብሔር ማስገዛት



# ፈተና ---- ውድቀት

ለውድቀት ዓይነተኛ ምክንያቶች (Thomas [Bishop]):-

- የማኅበራዊ ክህሎት እጥረት (Lack of social skills)
- የትኩረት መበታተን (To scattered a focus)
- የነገሮች አለመጣጣም (Mismaching of elements)
- በሌሎች ነገሮች ጥገኛ መሆን (Depending on others)
- የድፍረት ማጣት(Absence of commitment)
- የግል ሥነ-ምግባር ማነስ(Lack of self discipline)
- በሌሎች እንቅፋቶች (Hidden Barriers) እድሜ፣ጾታ፣ትምህርት፣የኑሮ ዕድገት